ሳምንታዊ ዜና (ሐምሌ 19 ቀን 2000 ዓ. ም.)

**ወያኔ እጅ መንሻ የሚሆን ስፊ መሬት ለጅቡቲው ፕሬዝዳንት እስማኤል አዲስ አበባ ውስጥ መስጠቱ ታወቀ፣ በጅቡቲ ወደብ ተጨማሪ 225 ሚሊዮን ብር ክፍያ ተጠየቀ፣1 እሽት በቆሎ 2 ብር እና ከዚያም በላይ እየተሸጠ ነው፣ የወያኔ ባለሥልጣናት በሕዝብ ሀብት ቁማር እየተጫወቱ መሆኑ ተጋለጠ፣ የወያኔ አባል የአፋር ክልል ፕሬዝዳንት በጠና ታመሙ፣ የኑሮ ውድነቱ የፈጠረው ጫና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሱዋል፣ ቴዲ አፍሮ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ መወሰኑ የሕግ ባለሙያዎችን አስቆጣ »»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዝርዝር ዜና ያንብቡ..........................**

ወያኔ ለመኖና አጨብጭቦ አሰብ ወደብን ካስረከበና ከሻዕቢያጋር ፀብ ውስጥ ከገባ በኋላ በጅቡቲ ወደብ እየተጠቀመ ቢሆንም በየጊዜው በሚደረገው የወደብ ታሪፍ ጭማሪ የተነሳ ለከፍተኛ ኪሣራ እየተዳረገ ሲሆን ሀገሪቷና ሕዝቦቿም እጅግ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እየወደቁ መሆኑ ተጋለጠ::

ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በጅቡቲ መንግስት በኩል የወደብ ታሪፍ ጭማሪ የተደረገ ሲሆን፣ ወያኔ ለጥቂት ቀናት በሱማሊያ በኩል ሞምባሳ ወደብ ለመቀጠም የሞከረ ቢሆንም ከጥቅሙ ጉዳቱ በማመዘኑ ተመልሶ የጅቡቲ መንግስት እግር ስር ወድቆ ወደብ መጠቀም የጀመረ ሲሆን፣ ሰሞኑንም የታሪፍ ጭማሪ በመደረጉ እየተለማመጠ መሆኑን የተለያዩ ዘገባዎች እያጋለጡ ናቸው::

በቅርቡ የጅቡቲ መንግስት ባደረገው የታሪፍ ጭማሪ የተደናገጠው ወያኔ ሁኔታውን ለማለዘብና ጊዜው እንዲራዘምለት ለመለመን የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ግርማ ብሩን ወደ ጅቡቲው ፕሬዝዳንት ልኮ የታማፀነ ሲሆን፣ ጅቡቲም ከኢትዮጵያ አትክልትና ጫት የምትወስድ በመሆኑ ለጊዜውም ቢሆን ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የእሽታ መልስ የሰጡ መሆኑን ተዘግቧል::

ምንም እንኩዋን የተሰጠው የጊዜ ገደብ ምን ያህል እንደሆነ ባይታወቅም በግርማ ተላላኪነት በጉ ምላሽ የሰጡት የጅቡቲው ፕሬዝዳንት እስማኤል ኦማር ጌሌህ ጭማሪ መደረጉ አይቀሬ መሆኑን ግን አፅንኦት ሰጥተው እንደገለፁት የጠቆሙት ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ቢበዛ ከ1 ወር በላይ የሚሰጧቸው አይመስለንም ሲሉም ግምታቸውን ሰጥተዋል::

ጅቡቲ የወደብ ጭማሪውን ቀነ ገደብ እንድታራዝም ለማድረግ ተልኮ የሄደው ግርማ ብሩ ለጊዜው የተሳካለት መሆኑን የተረዱት የወያኔው መሪዎች እንደገና እጅ መንሻ እና መለማመጫ ስፊ መሬት ቤት መስሪያ ይሆናል በሚል ለጅቡቲው ፕሬዝዳንት እስሜኤል ኦማር ጊሌህ በሌሉበት መሰጠቱ ታውቋል::

80 ሚሊዮን ሕዝብ ያላትን ሀገር ወደብ አልባ እንድትሆን ያደረገው ወያኔ በሰራው ስህተት አንዲትም ፀፀት የማይሰማው ቡድን ከመሆኑም በላይ ስለ አሰብ ወደብ የኢትዮጵያ መሆን የሚያነሳውን ሁሉ እንደጠላት እያየ እየገደለና እያሰረ መሆኑ የሚያሳዝን ነው ያሉት አንድ የቀድሞ የባህር ኃይል መኮንን ዛሬ የወደብ ታሪፍ ተጨመረ፣ናረ እየተባለ በሕዝብና በሀገር ሀብት የሚቀለደው ቀድሞ

በሩጫ ለሻዕቢያ አጎብድደው የተደረጉት ሁሉ ባይከናወኑ ኖሮ እንዲህ ያለ ውርደት ውስጥ አንገባም ነበር በማለት በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል::
እነ መለስ ዜናዊ በአዲስ አበባ ሰፊ መሬት የሰጧቸው የጅቡቲው ሬዝዳንት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ጥሪ ቢደረግላቸውም እንደማይመቻቸው በመግለፃቸው በኤምባሲያቸው አማካኝነት ቦታውን እንዲረከቡ መደረጉን የገለፁት ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች በወያኔ ስርዓት አልበኝነት የተነሳ ጐረቤት ሀገሮች ባኮረፉ ቁጥር ከመሀልና ከዳር መሬት እየቆረሰ መስጠት ልማዳቸው ሲሆን፣ በቅርቡም ለሱዳን ለም ሰፊ መሬት የተሰጠ መሆኑን አስታውሰው ይኸውም መሀል አዲስ አበባ ላይ መሰጠቱ ዞሮ ዞሮ እጅ መንሻ ነው ብለዋል::

ይህ የወደብ ጭማሪ ታሪፍ ተግባራዊ ሲሆን ሀገሪቷ በአመት በ22.5 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወይም ከ225 ማሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ የምታወጣ ሲሆን፣ አንድ የበቆሎ እሸት 2ብር እየገዛ ላለ ሕብረተሰብ ይህን ያህል ከፍተኛ ወጪ ሲጨመርበት መድረሻው ምን እንደሚሆን ይከብዳል ያሉት አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ የወያኔው ቡድን አንዳችም ሀገራዊና ሕዝባዊ ስሜት የሌለው በመሆኑ የሚያደርጋቸውና የሚፈፅማቸው በሙሉ በግዴለሽነትና በምን ቸገረኝነት ነው:: ለዚህም ነው በየጊዜው በሕዝቡ ላይ የኑሮ ጫና እየተፈጠረ ያለው ብለዋል::

ወያኔ ለሕዝቡ ቅንጣት ታክል የማያስብ ግድ የለሽ መሆኑን ያወቅነው ቀድሞ ቢሆንም በተለይ የረሀብ አደጋ እየተስፋፋ ባለበት በዚህ ወቅት ላይ የዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ሀገር ጥለው እንዲወጡ ማድረጉና ከውጭም ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የከለከለው ጭፍን ጥላቻ በሕዝቡ ላይ ስላለው ነው ያሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው አሁንም የወደብ ጭማሪው ተግባራዊ እንዳይሆን እየተለማመጠ ያለው ለህዝቡ አስቦ ሳይሆን ለራሱ ጥቅም መሆኑን በቁጭት ገልፀዋል::

በአሁን ሰዓት የጅቡቲ መንግስት ከወደቡ ታሪፍ በተጨማሪ ወደብ የገባ ማንኛም የኢትዮጵያ ዕቃ በ7 ቀናት ውስጥ መነሳት እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን፣ ይህ ባይፈፀም ሊወረስ ወይም እጥፍ ሂሳብ ሊያስከፍል እንደሚችል በግልፅ ያስቀመጠ ከመሆኑ ጋር በርካታ የሀገሪቱ አስመጪና ላኪ ነጋዴዎች በከፍተኛ ስጋት ውስጥ ከመውደቃቸውም በላይ በአሁኑ ጊዜ የሀገሪቷ ኢኮኖሚ ከድጡ ወደ ማጡ እየገባ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል ሲሉም እያማረሩ ይገኛሉ::

ሀገርና ሕዝብ በችግርና በችጋር እንደብራና ተወጥረው ባሉበት በዚህ ወቅት የወያኔ ሹመኛ የሆኑ ባለሥልጣናት ከቱጃሮች ጋር ቁማር እየተጫወቱ የሕዝብ ገንዘብ መቀለጃ እያደረጉት መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋልጧል::

የሀገሪቱ ሕዝብ የበቆሎ እሸት 2ብር አንድ ፍሬውን እየገዛ ቀምሶ ለማደር እየተውተረተረ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔ ከፍተኛ የጦር አዛዦችና ከፍተኛ ባለስልጣናት በሀገር ውስጥ ካሉ ቱጃሮችና ከጅዳና ዱባይ ከሚመጡ ታላላቅ የውጭ ሀገር ሀብታሞች ጋር ቁማር እየተጫወቱ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች እያንዳንዱ ባለሥልጣን በጥሬ ገንዘብ በሳምሶናይት ይዞ እንደሚገባም አጋልጠዋል::

ከአዲስ አበባ ወደ ናዝሬት በሚወስደው መስመር ላይ ከደብረዘይትና ሞጆ መካከል በሚገኘው አሮሰ ተብሎ በሚጠራው ሆቴል ውስጥ የሚካሄደው ይኸው ቁማር ታዋቂ ግለሰቦችና ባለሥልጣናት እንዲሁም ከውጭ ሀገር የሚመጡ ቱጃሮች ብቻ የሚጠቀሙበት ሲሆን፣ ለዚሁ ጥበቃ የሚያገለግሉ በሆቴሉ ባለቤት ትዕዛዝ ውጭ ሀገር ድረስ ተልከው የሰለጠኑ ኮማንዶዎች ያሉት መሆኑን የገለፁት ምንጮች ሕዝብ በየቦታው በረሀብና በኑሮ ውድነት እንደቅጠል እየረገፈ እነሱ ገንዘብ ተርፏቸው ቁማር መጫወቻ ማድረጋቸው የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ከመሆኑም በተጨማሪ ማሰቢያ የሌላቸው መሆኑን በግልፅ ያሳየ ሲሆን ስርዓቱም ምን ያህል ብልሹ እንደሆነ የተጋለጠበት ነው ሲሉ የሀገሪቱ ህዝቦች በንዴትና በብስጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡

ዛሬ አንድ ኩንታል የተበላሸ በቆሎ ዋጋ ከ700 ብር በላይ እያናጠረ ባለበት፣ የበቆሎ እሸት እንኩዋን አንዷፍሬ 2 ብር እየተሸጠ ባለበት በዚህ ቀውጢ ቀን ምድረ ባለሥልጣን በሕዝብ ስም በብድርና በልመና የሚመጣውን ገንዘብ እየመነዘሩ ለቁማር መጫወቻ ማዋላቸው የሚገርም ብቻ ሳይሆን የሚያንገበግብ ነው ያሉት ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር በየትኛውም መሥፈርት ቢሆን እንዲህ ያለ ወንጀል ሲሰራ መስማቴ በሀገሪቷ ታሪክ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ሲሉ በአግራሞት ገልጸዋል፡፡

እርዳታ ሰጪዎችን ከሀገር ውስጥ እያባረሩ፣ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ እየከለከሉ፣ ምንም ረሀብ በሀገሪቷ እንዳልተከሰተና ቢኖርም እነሱ ማከናወን እንደሚችሉ በሀሰት ፕሮፖጋንዳቸውን የሚነዙት እነዚህ የወያኔ ባለስልጣናት ሕዝቧን ለድህንነት ሀገሪቷን ለምድረ በዳነት እየዳረጉ ያሉት ምን መተማመኛ እንዳላቸው ግርም የሚል ፍፁም የሀገራዊ ራዕይ የሌላቸው አውሬዎች ናቸው ሲሉም ገልፀዋል፡፡

ከዋናው መሪ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ጀምሮ እስከታች ዝቅተኛው ካድሬ ድረስ የሀገሪቷን ሀብት እያሟጠጡ ያሉት አልበቃ ብሏቸው ዛሬ የወያኔ ጄኔራሎችና ባለሥልጣናት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ከሚመጡ ቱጃሮች ጋር ቁማር መጫወት ማለት ምን ያህል ገንዘብ እንደሚዘርፉ የሚያመለክት ነው ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

ከአንዱ የወያኔ አባል አንዱ የማይሻልበት ስማቸው እንጂ ምግባራቸው አንድ አይነት የሆኑት እነዚሁ ግለሰቦች የሀገሪቷን ሀብት ከማራቆታቸውም በላይ እንዲህ ያለ ወንጀል ሲፈፅሙ እየታየ ዝም መባላቸው አሳፋሪ ነው ያሉት አንድ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ጉልማሣ እኔ ሁኔታውን ስመለከት የሚታየው ትዕይንት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ አይመስልም ሲሉም ትዝብታቸውን ያጋራሉ፡፡
የወያኔ ሹመኛው የሕወሓት አባሉ የአፋር ክልል ፕሬዝዳንት እስማኤል አሊሴሮ በጠና በመታመሙ በክልሉ መደበኛ 7ኛ ጉባኤ ላይ ሳይገኝ መቅረቱ ተጋለጠ፡፡

በውስጥ ደዌ ተጠቂ የሆነው ይኸው የአፋር ክልል ፕሬዝዳንት የሕወሓት አባሉ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በድብቅም ሆነ በይፋ አረብ ሀገራት ለሕክምና ሄዶ እንደነበር የገለጹት ምንጮች የአሁኑ ግን ከፍተኛ በመሆኑ ይህንን የመሰለ ወሳኝ ጉባኤ የሚሉትን በክልሉ 7ኛ ጉበኤ ላይ አለመገኘቱ የሕመሙን ከባድነት የሚያሳይ ነው ካሉ በሁዋላ ግለሰቡ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ በሳዑዲ ሕምክና ሲደረግለት ስለነበር ምናልባትም አሁንም ወደዚያው ሳያመራ አይቀርም ሲሉ ግምታቸውን ገልፀዋል::

ከዚህ ቀደም የወያኔ ደህንነትና የፌዴራል ፖሊስ በጥምረት ግለሰቡን በሌብነት ጠርጥሮ ለማሰር እቅድ አውጥቶ የነበረ ቢሆንም በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ የዳነ ሲሆን፣ በአሁን ሰዓት በክልሉ የሚገኘውን የጨው ማዕድን ለሕወሓት ጄኔራሎች አከፋፍሎ እየተጠቀሙበት እንደሚገኝም ምንጮቹ አጋልጠዋል::
ሳሞራ የኑስ፣ ሳዓረ መኮንንና ሌሎችም የሕወሓት ጄኔራሎች የጨው ማምረቻ ጉድጓድ በዚሁ በሕወሓት አባል በአፋር ክልል ፕሬዝዳንት እስማኤል አሊሴሮ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ይህንንና ሌሎችንም ጥቅማ ጥቅሞች ለወያኔ ባለስልጣናት በመሰጠቱ 17 ዓመት የክልሉ ፕሬዝዳንት ሆኖ ያገለገለ ግለሰብ መሆኑን አጋልጠዋል::

የወያኔ ባለሥልጣናት በሕዝብ ሀብት ያሻቸውን እየሰሩ ሕዝቡ በየቀኑ በኑሮ ውድነትና በችጋር እየረገፈ መሆኑ ከተለየዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በአዲስ አበባ ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ የኑሮ ውድነቱ እያየለ በመምጣቱና ከወትሮ በተለየ የሸቀጦች ዋጋ እያሻቀበ መምጣቱ የታወቀ ሲሆን 2 ብር ከ25 ሲሸጥ የነበረው ቲማቲም እንኩዋን ወደ 5ብር ከ50 ያደገ ሲሆን፤ እስከ ቅርብ ቀናት ድረስ 1ብር ከ75 ሲሸጥ የነበረው ቀይ ሽንኩርት 5 ብር የገባ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል::

በአሁን ሰዓት በልቶ ከሚያድረው ይልቅ የማይበላው እየበለጠ በሚገኝበት በዚህ ሰዓት የወያኔ ባለሥልጣናትና ካድሬዎቹ ከሕዝብ በዘረፉት ገንዘብ ቦታና ቤት ለመግዛት እየተሻኮቱ መሆኑን ያስተዋሉ አንድ አዛውንት ሕዝብ አንድ ቀን እንደ ጉርፍ ሙላት ተነስቶ ያጥለቀለቃቸው ጊዜ ምን ምላሽ ሊሰጡ እንደሚችሉ እናያለን:: አሁን ግን እያማረጡ ከመብላት ጀምሮ እስከ ቤት ግንባታ የተቆጣጠሩት እነሱ ጀሌዎቻቸው ብቻ ናቸው ብለዋል::

የጤፍ ዋጋ ከወትሮው ጨምሮ 1300 ብር መሸጥ መጀመሩን የገለፁት የአይን እማኞች ሌሎች ሸቀጦችም ከወትሮው በተለየ መልኩ ዋጋው እያሻቀበ መሆኑን አክለው ገልፀዋል::

ወያኔ ወትሮም ለሕዝብና ለሀገር ቅንጣት ታክል ደንታ የሌለውና ማሰቢያ የሌላቸው ግለቦች ጥርቅም ነው ያሉት አንድ አዛውንት ሕዝብ በረሀብ በየሜዳው እየወደቀ እያዩ ማሾፋቸው የሰው ፍጡር መሆናቸውንም እጠራጠራለሁ ሲሉ ምሬት በተቀላቀለበት ቁጣ ገልፀዋል::

የኢትዮጵያን ሕዝብ ትዕግስቱን እንደ ሽንፈት የቆጠሩት እነኚሁ ወያኔዎች ሕዝቡ ተርቦ ትንፍሽ አለማለቱና አንገቱን ደፍቶ መኖሩን እያዩ ቢሣለቁም አሁን ግን በቅርብ ቀን ውስጥ የሚፈጥረው ማዕበል እናየዋለን ሲሉም ስጋታቸውን እየገለፁ ናቸው።

በአዲስ አበባ ባለፈው ሳምንት አንዲት እናት 50 ኪሎ ጤፍ አስፈጭተው ተሸክመው ወደ ቤታቸው በመሄድ ላይ ሳሉ አራት ጉረምሶች ቤተሰቦቻችን ሊሞቱ በመሆኑ እናዝናለን በማለት ይዘውባቸው የጠፉ ሲሆን፣መርካቶ እና ሌሎች አካባቢም የቀን ዘረፋ መጀመሩ የኑሮ ውድነቱ እየናረ መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እየገለፁ ይገኛሉ።

በተለይም ከክረምቱ ጋር ተዳምሮ የኑሮ ውድነቱ ማሻቀብን ፍፁም ያልተቋቋመው ደሀው ሕብረተሰብ በየሜዳው ላይ እየወደቀ መታየቱ የየዕለት ተግባር ሲሆን፣ እነ ወያኔዎች ግን ችግር በሀገሪቱ እንዳልተፈጠረ አስመስለው አሁንም ሲለፍፉ የመታየታቸው ጉዳይ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ብለዋል።

ለጋሽ ድርጅቶች የችግሩንና የረሀቡን አሳሳቢነት ተረድተው ለህዝቡ ፈጥነው ለመድረስ ሙከራ ቢያደርጉም ወያኔ በሚፈጥረው ጫና የተነሳ ወደ ሀገር ውስጥ ለመግባት የተቸገሩ ሲሆን፣ ቀድመው ገብተው የነበሩትም ለጋሽ ድርጅቶች ቢሆኑ በሚደርስባቸው ወከባና እንግልት የተነሳ ሀገሪቱን ጥለው እየወጡ ናቸው።

ይህ የወያኔ አረመኔ ቡድን ለሕዝቡ እርዳታ እንዳይሰጡ የሚገቡትንና ሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ለጋሽ ድርጅቶች እያባረረ ከመሆኑም በተጨማሪ እራሳችንን እንችላለን በሚል የሚመጣውንም የእህል እርዳታ አንቀበልም እያለ በሕዝብ ሞት እየቀለደና እያሾፈ የሚገኝ ቡድን መሆኑ ታውቋል።

በመጨረሻም አረመኔው የወያኔ ካድሬ ዳኛ ልዑል ገ/ማርያም የተባለው ግለሰብ በቴዲ አፍሮ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ማሳለፉ ታወቀ።

እስከ ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ሲንከባለል ቆይቶ ሰኞ እለት የጥፋተኝነት ውሣኔ የሰጠው ይኸው ካድሬ በዕለቱ አዛኝ መስሎ ለመታየት ቢሞክርም ማንነቱ ግን ይፋ የወጣው ቀድሞ ነው ያሉት ችሎቱን ሲከታተሉ የቆዩት አንድ የሕግ ባለሙያ አቃቤ ሕግ ተሳስቶ ያቀረበውን ማስረጃ ፎርጅድ አሰርተህም ቢሆን አቅርብ ብሎ ማዘዙ ሳያንሰው እምነት የለኝም ያለውን ኩባዊ መጽሀፍ ቅዱስ ይዘህ ማል በማለት አስገድዶ ማስመስከሩ በአለም ላይ የመጀመሪያ አሳፋሪ ታሪክ ነው ብለዋል።

በሕግ ባለሙያነት ሽፋን የካድሬነት ተልዕኮውን እየተወጣ ያለው ይኸው ልዑል ገ/ማሪያም የልጆቹን እናት ፈትቶ ሌላ ከዕድሜው 30 ዓመት በታች ከሆነች ኮረዳ ጋር የሚዳራው ይኸው ግለሰብ ለቤተሰብ አክብሮት የሌለው ፍፁም ማህበራዊ ህይወቱ ብልሹ መሆኑን የገለጹት እኚሁ የህግ ባለሙያ

በዳኝነት ቦታ ላይ መቀመጡ ስርዓቱ የወረደና የዘቀጠ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም ከእንግዲህ ወደ ፍርድ ቤቶች ብቅ አልልም በማለት እንባ እየተናነቃቸው ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

በዕለቱ እንደተለመደው ፍርድ ቤት በአድናቂዎቹና በወዳጅ ዘመዶቹ የተጥለቀለቀ ሲሆን 3 ሰዓት ላይ የተጀመረው የፍርድ ሂደት የወያኔ ካድሬው ዳኛ ተብዬው ልዑል ሰርቶ የመጣውን ውሳኔ ይህንኑ የቴዲን ሀጢያት ያበዛበትን ጽሁፍ «ጥፋተኛ በመሆንህ ተከላከል» ብሎ ያነበነበ ሲሆን፣ ውሳኔን ከሰጠ በኋላ ወደ እውቁ ቴዲ አፍሮና ጠበቃው ዞሮ ለመቼ ይሆንላችሁ? በማለት ቢጠይቃቸውም እንደጀመርከው መጨረስ ትችላለህ የፈለግክበትን ቀን መቅጠር ትችላለህ በማለት ምላሽ ሰጠተዋል፡፡

በመልሳቸው የተበሳጨው ይኸው ወያኔ ለመስከረም 29 ቀን 2001 ዓ.ም የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ ይዛችሁ እንድትቀርቡ በማለት የችሎቱ ውሎ ሊጠናቀቅ ሲል እውቁ ኢትዮጵያዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ቀኝ እጁን ወደ ላይ ከፍ አድርጐ «የኢትዮጵያ አምላክ ፍርድ ይሰጠኛል» በማለት በንዴት እንባውን ሲያፈስ በችሎቱ የነበሩት ፖሊሶች ሳይቀሩ በእንባ ሲራጩ ታይተዋል፡፡

በግቢው ውስጥ ሲጠባበቁ የነበሩት አድናቂዎቹም ውሣኔውን ሲሰሙ መሬት ላይ እየወደቁ ሲያለቅሱ እንደነበርና ከመሀከላቸውም 5 ያህሉን የፌዴራል ፖሊሶች አፍሰዋቸው ወደ አልታወቀ ቦታ የወሰዱዋቸው መሆኑን የአይን እማኞች ገልጸዋል፡፡

የወያኔ ባለሥልጣናት እርስ በእርስ ተጣልተው የከተማውን ሕዝብ ሲያምሱ ማምሸታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለጸ፡፡
ከአዲስ አበባ 110 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ፍቼ ከተማ ውስጥ ኮማንዶ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የኦህዴድ ካድሬ የሆነው አብዱ የተባለው ግለሰብ እራት ለመብላት አለም ሆቴል ሲገባ ለምን አየኸኝ በማለት አንድ የመከላከያ ሠራዊት አባል የሆነ መኮንን በመሳደቡ በተነሳ ፀብ ከተማው ሲታመስ ያመሸ ከመሆኑም በላይ መኮንኑ እንደተገደለ የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

አብዱ የተባለው የናዝሬት ልዩ ዞን የፀጥታ ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ መኮንኑን በጥይት ከገደለ በኋላ አምልጦ ለፖሊስ እጁን የሰጠ ሲሆን፣ በከተማው አቅራቢያ ካምፕ መኖሪያቸው የሆኑት ወታደሮች በመኪና መጥተው ሕዝቡን በዱላና በጥይት ተኩስ ሲያሸብሩ ያመሹ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

ወትሮም ስርዓት አልበኝነት የነገሰበት ይኸው የወያኔ ስርዓት በሁለቱ ግለሰቦች ፀብ ምክንያት ሕዝቡን የቁም ስቅሉን ማሳየታቸው የሚያሳዝንና በርካቶቹም በማያውቁት ምክንያት በዱላ መደብደባቸው ሕግና ስርዓት እንደሌለ አመላካች ነው ሲሉም ነዋሪች በማማረር ይገልፃሉ፡፡

አብዱ የተባለው የኦህዴድ ካድሬ ለ3 ቀናት ያህል በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ በአባዱላ ገመዳ ትዕዛዝ ወደ ስራ ገበታው እንዲመለስ መደረጉን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቱዋል፡፡

በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የተጀመረው ሽኩቻ ተፅእኖው ወደ ሲቪል ካድሬች ጭምር እየተስፋፋ በመምጣቱ የተነሳ ሙዋች መቶ አለቃው የትግራይ ብሔር ተወላጅ ሲሆን ገዳይ ደግሞ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ካድሬው እራቱን ሊበላ ወደ ሆቴሉ በገባበት ወቅት እብሪት የወጠረው መቶ አለቃ እራሱ በፈጠረው ፀብ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል ሲል ዘገባው አብራርቷል::

በሠራዊቱ ውስጥም ቢሆን የተጀመረው የበላይነትና የበታችነት ስሜት በየጦሩ ውስጥ ውጥረት ነግሶ የሚገኝ ሲሆን፣ በተለይም በከፍተኛ መኮንኖች ዘንድ ተቀጣጥሎ እንደሚገኝ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመዋል::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ከወትሮው በተለየ መልክ በመከላከያ ዋና መምሪያ ውስጥ በከፍተኛ መኮንኖች መካከል ይኸው ጉዳይ ተቀጣጥሎ እስከ ቃላት መወራወር የደረሱ ሲሆን፣ ቁጥራቸው ያልታወቁ ከፍተኛ መኮንኖች በዚሁ ሳቢያ ለጊዜው ስራ እንዳይገቡ የታገዱ መሆኑን ጥቆማው ያስረዳል::

በተለይም የመከላከያ ሚኒስትርነት ቦታ ላይ የራሳቸውን ሰው ለማስቀመጥ እነ መለስ ዜናዊ እየሰሩ ባሉበት በዚህ ጊዜ ከፍተኛ መኮንኖቹ ቦታው የኦህዴድ በመሆኑ ለነሱ ሊሰጣቸው ይገባል በሚልም ሽኩቻው ተጡዋጡፎ እንደሚገኝ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

ይኸው ውዝግብ ከዚህ ቀደም በጦሩ ውስጥ ተከስቶ «የትግራይ የበላይነት አለ ወይስ የለም?» የሚል ግምገማ ተነስቶ የነበረ ሲሆን አለ የሚሉት ከጄኔራል እስከ ተራ ወታደር ድረስ ተለቅመውና ታስረው የተባረሩ ቢሆንም አሁንም ተመሳሳይ ጫና እየደረሰባቸው በመሆኑ ችግሩ ሊከሰት እንደቻለ የመከላከያ ምንጮች ጥቆማ ገልፆ በተለይ በመከላከያ መምሪያዎች ውስጥ የተነሳው ሽኩቻ ተቀጣጥሎ ወደ የጦሩ ክፍል በመድረሱ የወያኔ አለቆች በሰበብ አስባቡ በዓል አዘጋጅን በማለት የምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ የለበሱ የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ የሠራዊቱ አባሎችን በቴሌቭዥን እያቀረቡ ቅራኔውን ለማርገብ ሰሞኑን እየሰሩ መሆኑንም ምንጮቹ ጠቁመዋል::

በዚሁ ሣምንት ውስጥ የተሰመረበትን 3ኛ ዓመት አከበረ የተባለው በህወሀቱ ጄ/ል ሳዕረ መኮንን የሚመራው የሰሜን እዝ በዓል ላይ በሠራዊቱ ውስጥ የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ሲባል ብቻ የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ የምክትል መቶ አለቃና ወታደሮች ሰብስበው ቅስቀሳ ሲያካሂዱ መታየታቸው ችግሩ ምን ያህል ስር ሰድዶ እንዳስቸገራቸው አመላካች ነው ሲሉም ምንጮቹ አስረድተዋል::

በመጨረሻም ከ40 ዓመት በፊት የተነገነባውና ስራ ላይ የዋለው የሀገሪቱ የጦር አባሎችን የሚያስተናግደው ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ

ሁሉን ለራሴ  በሚል ሰፍሳፋ  ስሜት በ40  ሚሊዮን ብር ትግራይ  ውስጥ ዘመናዊ  ሆስፒታል ማስገንባቱ  ታወቀ።

እዳጋ ሐሙስ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በ40  ሚሊዮን ብር በርካታ  ሕሙማን የሚያስተናግድ የጦር ኃይሎች ሆስፒታል  ያስገነባው  ወያኔ የዕለቱ  የክብር  እንግዳ ተብሎ  አባዱላ  ገመዳ  የተገኘ ቢሆንም የበላይ ሆነው የተስተዋሉት የህወሀቶቹ ጄኔራል ሳሞራ የኑስና ሜጀር ጄኔራል  ሳዓረ መኮንን መሆናቸው  በሠራዊቱ  ውስጥ ያለው  ያለመተማመንን ጭምር ያንፀባረቀ ነው  ሲሉ የመከላከያ ምንጮች  ገልፀዋል።

አሁንም የበላይ  ነን የሚል መልዕክት ያስተላለፉት  የሕወሓቶች  ከፍተኛ መኮንኖች አባዱላን ከአዲስ አበባ ድረስ  አስጠርተው እንደ ጀሌ ከኋላ  አስከትለው ገትረው የዋሉት  ሲሆን፣  ሪቫን የመቁረጥና የክብር እንግዳ  ሆኖ የዋለው ጄኔራል  ሳሞራ  የኑስ  መሆኑን  ከምንጮቹ የተገኘው  ዘገባ ያስረዳል።